# ትምህርት 14፣ ጥምቀት

ወጣቱ ሐሚድ እንቆቅልሽ ሆኖበታል። ባለፈው ዓመት ህይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰጥቷል። በአዲሱ እምነቱም ጠንክሮ እያደገ ነው። ቅርብ ጊዜ ሌላ አማኝ "ከሰሞኑን መጠመቅ አለብህ" አለው። ይህም በሐሚድ አይምሮ ብዙ ጥያቄዎችን ፈጠረ፥




በዛሬው ትምህርት እያንዳንዱን የሐሚድ ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር።

## 'ጥምቀት ምንድነው?'

1. 'ጥምቀት' በቀጥታ ሲተረጐም በውሃ ውስጥ መነከር ወይም መጥለቅ ነው። መጥምቁ ዩሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ኢየሱስን ጨምሮ እንዴት ሰዎችን እንዳጠመቀ በአዲስ ኪዳን ላይ እናነባለን። በዚህም ዘመን የክርስቶስ ተከታዮች በወንዝ፣ በውሃ ማጠራቀሚያ፣ በሚፈስ ውሃ ስር ለተወሰነ ጊዜ በመቀመጥ ሊጠመቁ ይችላሉ።
   በህይወታችን በዚህ አስፈላጊ ስርዓት ውስጥ የምናልፈው በተደጋጋሚ ሳይሆን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የዚህ ስርዓት ስም ምንድነው? ________________________________________________

## 'መጠመቅ ያለብኝ ለምንድነው?'

2. የምንጠመቀው ጌታ ኢየሱስ ስላዘዘ ነው። እሱም እንዲህ አለ፥

   "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤" (ማቴዎስ 28፥19)

   ይህ አስፈላጊ ጥቅስ ስለሆነ እባክህ አሁን በቃልህ አሰላስለው።

3. ሐዋሪያው ጴጥሮስ ለክርስቶስ ትዕዛዝ ምላሽ በመስጠት፣ በእየሩሳሌም ለተሰበሰብ ብዙ ህዝብ *"ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤"* (የሐዋሪያት ስራ 2፥38) ብሎ ይነግራቸው ነበር። እንድጠመቅ በቂ ምክንያት የሚሆነኝ ምንድነው? (አንድ መልስ ብቻ ምረጥ)

   ______ ሀ) ማድረግ ስለምፈልግ

   ______ ለ) አማኝ ጓደኞቼ እንዳደርገው ስለሚፈልጉ

   ______ ሐ) ጌታ ኢየሱስ እንዳደርገው ስላዘዘኝ

## ‘ጥምቀት የሚያሳየው ምንድነው?’



ጥምቀት በጣም ልዩ እና አስፈላጊ ነው። ጥምቀት በአዲስ ኪዳን መሠረት የሚያሳየው፤

ሀ) እኔ በክርስቶስ አዲስ ሰው ነኝ

ለ) ኃጢያቴ ታጥቦልኛል

ሐ) የክርስቶስን ማህበረሰብ ተቀላቅያለው

ስለዚህ አስደናቂ እውነት እስኪ እንማር።

## ሀ) እኔ በክርስቶስ አዲስ ሰው ነኝ

4. አንዳንድ ሰዎች ውሃ ውስጥ ገብቶ ለመጠመቅ ፍርሃት አለባቸው። በጥምቀት ጊዜ ሰዎች በውሃ ውስጥ የሚሆኑት ለጥቂት ሰኮንዶች ብቻ ነው እናም አደገኛ ስላልሆነ አትጨነቅ። ወደ ክርስቶስ ዘወር ባልን ጊዜ ግን በህይወታችን የሆነው የምንተረጉምበት ምልክት ነው። ያለፈውን ኃጢያተኛ ፍጥረታችንን በመቅበር በኢየሱስ በሆነው አዲስ ህይወት መነሳትን ማሳያ ነው!

   ድርጊቱን ከትርጉሙ ጋር በመስመር አዛምዱ፤

| ድርጊት | ትርጉም |
|---|---|
| ሀ) ወደ ውሃ ውስጥ መግባት | 1. በክርስቶስ እንደገና አዲስ ሰው ሆኖ መነሳት |
| ለ) ከውሃ ውስጥ መውጣት | 2. አሮጌውን ፍጥረት መግደል |

5. ስለዚህ ጥምቀት አሮጌው ህይወት ማብቃቱን እና አሁን በክርስቶስ አዲስ ሰው መሆን ማሳያ ምልክት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤

   “እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።” (ሮሜ 6፡4)

ጥምቀት የሚያሳየው የመጀመሪያው እውነት ምንድነው?

[በክርስቶስ አዲስ ሰው መሆኔን / አሁንም በአሮጌው ኃጢያተኛ ፍጥረት ውስጥ እንዳለው]

6. ብዙ ጊዜ ሰዎች ለመጠመቅ ሲሄዱ የቀድሞ ልብሳቸውን ያደርጋሉ ይህም በኃጢያት የተሞላውን አሮጌ ህይወትአመላካች ነው። ከዚያም ከውሃው ሲወጡ የሚለብሱት ንጹህ ልብስ ደግሞ በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ህይወት ያሳያል።

**ተጠምቀህ ከሆነ፣ ከውሃው ስትወጣ የነበረህ ስሜት ምንድነው? በወይይትም ጊዜ ስለዚህ ለመናገር ተዘጋጅ::**

7. ከአፍሪካ የሆነው ፊራዝ ወደ ክርስቶስ የመጣው አንተ ቀድሞ ከነበርከበት ሃይማኖት ነው። ከጥምቀት በኋላ የተሰማውን በራሱ አንደበት እንዲህ ይገልጸዋል፡:

“ለአሮጌው ኃጢያታዊ መንገዴ የሞትኩ ያህል ይሰማኛል፣ ራሴን ለእግዚአብሔር ሰጥቻለው እናም አሁን እኔ አዲስ ሰው ነኝ። ጓደኞቼ የሚያውቁኝ ፊራዝ አይደለሁም ፣ ሰይጣንም የሚያውቀው አይደለሁም፣ ነገር ግን ይቅር የተባልኩ፣ ዳግመኛ የተወለድኩ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚገዛኝ አዲሱ ፊራዝ ነኝ። አሮጌው ፊራዝ ሞቷል፣ አዲሱ ደግሞ በክርስቶስ ህያው ሆኖ ይኖራል። ከውሃው ስወጣ አዲስ እንደሆነ ሰው እየተሰማኝ ነበር!”

ከላይ በቀረበው ሳጥን ውስጥ ‘አዲስ’ የሚለውን ቃል ፊራዝ ስንት ጊዜ ተጠቅሞታል? /ቃሉን አስምሩበት/

8. ጥምቀት የሚያሳየው የመጀመሪያው እውነት ምንድነው? እኔ በክርስቶስ ___________ ሰው ነኝ

## ለ) ኃጢያቴ ታጥቦልኛል

9. የሐዋሪያት ስራ 22፡16 ስለጥምቀት ሁለተኛውን እውነት ይነግረናል:
*"ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ።"*
በዚህ ጥቅስ መሠረት፣ ጥምቀት የሚያሳየው እውነት ምንድነው?



_____ ሀ) እኔ በክርስቶስ አዲስ ሰው ነኝ

_____ ለ) ኃጢያቴ ታጥቦልኛል

10. ከልምድ እንደምናውቀው፣ ከኃጢያት ለመንጻት መታጠብ (ዋና) ወይም ገላን መታጠብ (ጉሳል) እንኳን በቂ አይደለም። ውሃ ማጠብ የሚችለው ውጫዊ አካላችንን ብቻ ነው፣ ልብ እና ሕሊናችንን ማንጻት አይችልም። ይሁን እንጂ ጥምቀት ክርስቶስ በልባችን የሠራውን ውስጣዊ ማንጻት የሚያሳይ ኃይለኛ ውጫዊ ምልክት ነው። ይህም እንዲቻል እርሱ በመስቀል ላይ ሞቷል።

1ኛ ዮሐንስ 1፡7 አንብብ

በ1ኛ ዮሐንስ 1፡7 መሠረት፣ ከኃጢያት ሁሉ የሚያነጻን ምንድነው? _______________

11. በህይወት ዘመኑ ብዙ ሰዎችን ያጠመቀው ሐዋሪያው ጴጥሮስ፣ በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡18-22 ስለጥምቀት ጽፏል። ይህን ምንባብ መተርጐም ቀላል አይደለም። ነገር ግን ዋና ዋና ነጥቦቹ፣

- የእኛ መዳን በኢየሱስ ሞት (ቁጥር 18) እና ትንሳኤ (ቁጥር 21) ነው
- ውሃ በ(ቁጥር 20) ላይ ለኖኅ እንደሆነው፣ ለእኛም የመዳናችን ምልክት ነው (ቁጥር 21)።

ኃጢያቴ እንደታጠበልኝ የሚያስታውሰኝ ስርዓት የቱ ነው?

_____ ሀ) ጥምቀቴ _____ ለ) ሠርጌ _____ ሐ) ቀብሬ

## ሐ) የክርስቶስን ማህበረሰብ ተቀላቅያለው



12. በመጠመቃችን የክርስቶስን ዓለም አቀፍ የአማኞች ማህበረሰብ (የክርስቶስ አካል) በግልጽ እንቀላቀላለን። ከተለያየ ዘር የተሰባሰብን ወንዶችና ሴቶች ነን። *"እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና።"* (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)

ጥምቀት የሚያሳየው ሦስተኛው እውነት ምንድነው? የክርስቶስን _______________ ተቀላቅያለው

13. ጥምቀት ለአንተ ብቻ በግልህ የሚሆን አይደለም፣ ነገር ግን የአማኙን ማህበረሰብ ሁሉ የሚካተትበት ነው። እነሱም መጠመቅህን ይመሰክሩልሃል እናም በመጨረሻም አንተን እንኳን ደህና መጣህ ለማለት እነዚህን ቃላት ሊጠቀሙ ይችላሉ፣

"ወደ ጌታ ቤተሰብ እንኳን ደህና መጣ። አብረን በክርስቶስ አካል ውስጥ አባል ነን፤ የአንዱ ሰማያዊ አባት ልጆች ነን፤ አብረንም የእግዚአብሔርን መንግስት የምንወርስ ነን፤ እንኳን ደህና መጣህ እንልሃለን።"

- **በእግዚአብሔር በተመረጠ ህዝብ እንኳን ደህና መጣችሁ በመባላችን እንዴት የታደልን ነን! አሁን ቆምና በክርስቶስ ስላሉህ ወንድሞች እና እህቶች እግዚአብሔርን አመስግን።'**

14. ጥምቀት የሚያሳየው ሦስት እውነት ምንድነው? (ባዶ ቦታውን ሙላ)

ሀ) እኔ በክርስቶስ ________ ሰው ነኝ

ለ) _______________ ታጥቦልኛል

ሐ) የክርስቶስን ማህበረሰብ _____________

ሐሚድ እነዚህን እውነቶችን ለመማር ጓጉቷል። በመቀጠልም የጠየቀው፣

## 'ጥምቀት በጣም አስፈላጊ ነውን?'

15. ጥምቀት በጣም አስፈላጊ ነው ? ለሚለው መልሱ አዎ የሚል ሆኖ ምክንያቱ ደግሞ የኢየሱስ ትዕዛዝ በመሆኑ ነው ። ( ዝርዝሩን በአስተማሪዉ የዉይይት ጊዜ ውስጥ ይገኛል )

16. በመጠመቃችን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መሆናችንን በኩራት እናሳያለን። ይህንንም በክርስቶስ ለሆኑ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን በመንገር ደስ ይለናል። በጥምቀትህ ላይ 'የአንተን ምስክርነት እንድትሰጥ' ምንአልባት ትጠየቃለህ። ይህ ማለት ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወትህን እንደለወጠው በግልጽ መናገር ነው።

ይህንንም አሁን እንሞክር። በጥምቀትህ ላይ ምስክርነትህን እየሰጠክ እንደሆነ አስብ። መሪው "ኢየሱስ ክርስቶስ <u>በአንተ</u> ህይወት ያደረገው ለውጥ ምንድነው?" ብሎ ቢጠይቅህ፣ አንተ ምን ትላለህ?

የምትናገረውን ጻፍና ለውይይት ተዘጋጅ። ከፈለግህ ደግሞ በትምህርት 2 ጥያቄ 15 ላይ የጻፍከውን አመሳክር። ነገር ግን እዚህ ጋር በዝርዝር ጻፍ።

______________________________________________

______________________________________________

__________________________________

17. ሀ) ጥምቀት በጣም አስፈላጊ ነውን? [አዎ/አይደለም]

ለ) ጥምቀት የክርስቶስ መሆንህን የምታሳይበት በጣም አስፈላጊ ምልክት ነው? [አዎ/አይደለም]

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሐሚድን በጥምቀት ላይ ያሉ የተለያዩ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረናል። አሁን ወደ እሱ የመጨረሻ ጥያቄ መጥተናል።



## 'መጠመቅ ያለብኝ መቼ ነው?'

18. አንዳንድ ክርስቲያኖች ልክ ክርስቶስን እንደተቀበልክ መጠመቅ አለብህ ብለው ይመክራሉ። ሌሎች ደግሞ እምነትህ እስኪጠነክር መቆየት አለብህ ይላሉ። የእነሱን ምክር ስማ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ የሚለውንም አድምጥ። በዚህ አስፈላጊ እርምጃ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ ይመራሃል። ትክክለኛውም ጊዜ ሲደረስ በልብህ ይሰማሃል፡

ሳትዘጋጅ ሰዎች ወደ ጥምቀት እዳይገፋፉህ አድረግ። አግዚአብሔርም ጊዜው አሁን ነው እያለ ከነገረ ወደኋላ አታፈግፍግ፡

ከታች ከቀረቡት ተግባራት ውስጥ መልካም የሆነው የቱ ነው? (ሁለት መልስ ምረጥ)

_____ሀ) ለአንተ የሚጠነቀቅልህ የጥበበኛ አማኝ ምክርን ስማ

_____ለ) የሚስከትለውን ስለምትፈራ ባትጠመቅ ይሻላል

_____ሐ) መጠመቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ አስብ

_____መ) እግዚአብሔር እንደተናገረህ የተሰማህ ጊዜ ተጠመቅ

19. ለአንተ ግድ የሚለው ጥበበኛ አማኝ ስለ ጥምቀት መልካም ምክር ይሰጥሃል። አንዳንድ አማኞች ደግሞ ጥበብ የጎደለው የጥምቀት ስርዓትን እንደሚያዘጋጁ እወቅ እና አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥምቀትን ለስማቸውን እንደ ማስታወቂያ ይጠቀሙበታል። ስለዚህ ለአንተ ስርዓተ ጥምቀትን የሚያመቻችልህ የምታምነው ሰው ፈልግ። ስለአንተ መጠመቅ መልካም ምክር ሊሰጥህ የሚችል ሰው ታውቃለህ? ______________ የሚመችህን ሰው ማግኘት ካልቻልክ አማካሪህን ጠይቅ።

20. ለእኛ ለአማኞች ጥምቀት ምን ማለት እንደሆነ አስቀድመን ተምረናል። ለማያምኑ ዘመዶቻችን ግን ፋይዳው ምንድነው? ለእነሱ ጉዳት እና እፍረትን ያመጣ፣ በአደባባይ የተለያየንበት ምልክት አድርገው ይወስዱታል።

ስለዚህ መጠመቅ ያለብን እንዴት ነው? (አንዱን ምረጥ)

______ ሀ) ለራሳችን ደህንነት በመስጋት፣ በፍርሃት

______ ለ) ለቤተሰቦቻችን ካለን ፍቅር የተነሳ፣ በጥንቃቄ

21. ከማያምኑ ዘመዶቻችን የተነሳ መጠንቀቅ እና ቅድመ-ጥንቃቄ ማድረግ ጥበብ ነው። የእኛ መጠመቅ ዜና በዘመዶቻችን ላይ ከባድ እፍረትን እንዳያመጣ ለማስረገጥ፣ ምን ቅድመ-ጥንቃቄ መደረግ እንዳለብት ታስባለህ? (ሃሳብህን ጻፍና ለውይይት ጊዜ ተዘጋጅ)


________________________________________________

______________________________

22. ሚስቱ ወይም ባሏ የክርስቶስ ተከታይ ላልሆኑ አማኞች ምን ምክር ትሰጣለህ? አማኙ አሁን መጠመቅ ነው ያለበት ወይስ የትዳር አጋራቸው ክርስቶስን አምነው ሲመጡ፣ አብረን እንጠመቃለን በሚል ተስፋ መጠበቅ? (ሃሳብህን ጻፍና ለውይይት ጊዜ ተዘጋጅ)

________________________________________________

________________________________________




| **የትምህርት 14 ተግባራዊ ስራ** |
|---|
| እስከ አሁን ካልተጠመቅህ፣ በጥያቄ 19 ላይ የጠቀስከው ሰው ጋር በመሄድ ተነጋገርበት። መቼ እና እንዴት መጠመቅ እንዳለብህ የእነሱን ምክር አግኝ። የጌታንም ምክር ጠይቅ። |

## የትምህርት 14 ክለሳ

1. በቃል ያጠናህውን ጥቅስ ጻፍ፡ “እንግዲህ ሂዱና ______________________________ __________________________________ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤” (ማቴዎስ ___፡____)

2. መጠመቅ የሦስት ነገሮች ምልክት እንደሆነ ተምረናል። እነሱም ምንድናቸው?

   ሀ) ‘እኔ ____________ አዲስ ሰው ነኝ’

   ለ) ‘______________ ________________’

   ሐ) ‘የክርስቶስን _____________ ተቀላቅያለው’

3. መጠመቅ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? (ከጥያቄ 15 -17 በመከለስ አንዱን መልስ ምረጥ)

________በጣም አስፈላጊ ነው          ________አስፈላጊ አይደለም